# የለም፣ ዓባይማ ይገደብ፣ መገደብም አለበት፤ እንኳን በገንዘባችን በደማችንና በሕይዎታችን፣ <u>ግን.......?!</u>

### ዓባይ ለዘላቂው ጥቅማችን የምንታገልለት ተፈጥሮኣዊ ጥሪታችን፣ ዓባይ የፖለቲካ ለውጥ ለማስገኘት የወቅቱ መታገያችን!

*የግል አስተያየት፡- ከአያል ሰው ደሴ (ክፍል-ሁለት)*

በአሁኑ ጊዜ የዓባይን መገደብ የሚቃወሙ ወገኖች ለተቃውሟቸው የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ:: ከነዚኽ መካከል *“ይኽ እቅድ ቀደም-ሲል ጨርሶ ያልታሰበበትና በመካከለኛው-ምሥራቅና በሰሜን አፍሪቃ 'የአረብ ፀደይ (አረብ ስፕሪንግ)' በሚል የሚታወቀው ሕዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ጨቋኝና አምባ-ገነን ገዥዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠራርጎ ማስወገድ በመቻሉ የተደናገጠው የወያኔ አገዛዝ ይኽ አዲስ የሕዝብ ቁጣ በኢትዮጵያም እንዳይደገም ከመራድ የመነጨ፣ ብሶት ያንገፈገፈው ሕዝባችን ለለውጥ ያለውን መነሣሣት ለማዘናጋትና አቅጣጫ ለማስቀየር ታስቦ የተደረገ የማጭበርበርና የብልጣ-ብልጥ እርምጃ ነው፣ ለዚኽም ማስረጃ የሚሆነው 'የአምስት-ዓመት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ' በተባለው ላይ ጨርሶ አልተጠቀሰም ነበር፤ ... ይኽ ብሔራዊ-ስሜት-አልባ የሆነ አገዛዝ ዓባይን የመሰለ አገራዊ ጠቀሜታ ያለው የተፈጥሮ ሃብት ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል አስቦ ይሠራል ማለት የዋኀነት ነው፤ ... የአገዛዙ መሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዓባይ መገደብ ያለውን ልባዊ ምኞት ስለሚያውቁ የሕዝቡን ብሔራዊ ስሜት በማነሣሣት የአገር-ፍቅር ያለው መስሎ ለመቅረብና በተለይ ከአገር-ወዳዱና አንድነት ፈላጊ ከሆነው ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ድጋፍ ለመሻት፣ እንዲሁም በዚኹ ሰበብ የሕዝቡን ገንዘብ በመዝረፍ ለራሣቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ነው፤ ግድቡን ለመሥራትም ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ ተቋራጮች የአገዛዙና ከአገዛዙ ጋር ቁርኝት ያላቸው ድርጅቶች ስለሚሆኑ እነሱኑ ለመጥቀም ነው፣... ግድቡ ሆን ተብሎ ከሱዳን ጠረፍ አፍንጫ ሥር መደረጉ ለጥቃት እንዲጋለጥና ያን አደጋ ገዥዎቹም ስለሚያውቁት ለውጭ ጫና በማጎንበስ የሚታወቁት የወያኔ መሪዎች ይኽን ግድብ ደፍረው ተግባራዊ ሊያደርጉት አይችሉም፣ ... ወያኔ አማራን ለማዳከም ካለው መሠሪ አቋም የተነሣ ግድቡ ከ'አማራ ክልል' ወጥቶ በ'ቤኒሻንጉል ክልል' እንዲሆን ተደርጓል፣ ... ኢትዮጵያ ዓባይን ለመገደብ አቅሙም ችሎታውም እንደሌላት እየታወቀና አስቀድሞ ከግብፅና ከሱዳን ጋር ድርድር ሣይደረግ ዓባይን ለመገደብ ማሰብ ግብፅና ሱዳን (ይበልጥ ግን ግብፅን) ለጦርነት መጋበዝ ይሆናል፤ ....”*፣ እንዲያውም *“አገዛዙ ኢትዮጵያ ለግብፅ ወረራ እንድትጋለጥና ሕዝቧን ለማይቋቋመው ወታደራዊ ዘመቻ ለመዳረግና እልቂት ውስጥ ለመጨመር ሆን ተብሎ ታስቦ የተደረገ ተንኮል ነው፣ ...”* ወዘተርፈ፣ ወዘተርፈ፣ የሚሉ ይገኙባቸዋል::

ከሞላ-ጎደል የሁሉም ምክንያቶች በአብዛኛው ነገሮችን ሁሉ ሰፍኖ ከቆየው በተቃውሞ ላይ ከተመሠረተውና በእሱም ዙሪያ ከሚያጠነጥነው የፖለቲካ ቅኝታችን አኳያ ከማየትና እሱንም መሠረት ካደረገ አስተሣሰብ፣ የኢትዮጵያን ዘለቄታዊና ስትራቴጂካዊ ጥቅም ለጊዜው በሥልጣን ላይ ካለውና እንዲለወጥ ከምንታገለው አገዛዝ ለይቶ ማየት ካለመቻል፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የአገዛዙ ባኅሪና ታሪክ የወለዳቸው ጥርጣሬዎችን የተመረኮዙ ሲሆኑ አብላጫዎቹ ግን በትክክለኛ መረጃና እውቀት ላይ ያልተመሠረቱ በግልብ ስሜት ላይ የተንጠለጠሉ፣ በአጭሩ የዓባይ ግድብ ለኢትዮጵያ ያለውን ፈርጀ-ብዙ ትርጉምና እርባና በቅጡ ካለመገንዘብ የመነጩ ናቸው ማለት ይቻል ይመስለኛል:: በአጭሩ ይኽ አገዛዝ እንዲለወጥ ያለን ከፍተኛ ስሜትና ፍላጎት ግድቡ ለኢትዮጵያ ባለው (ሊኖረው በሚችለው) ትርጉምና ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ላይ ገዥነት እንዲኖረው ወይም እንዲያጠላበት

በመደረጉ፣ አንዳንድ አገር-ወዳድ ወገኖች ሣይቀሩ ይኸ ግድብ መሠራቱን በግልጥ እስከ-መቃዎም አድርሷቸዋል።

የሆነ ሆኖ ግድቡን ለመቃወም ከተሰጡት የተለያዩ ደረጃዎች ካሏቸው ምክንያቶች መኻል ከቅጥ-ማጣቱ አደገኝነቱ ያመዘነውና መሠረታዊ የአስተሣሰብ ድኅነት የምለው፣ በግሌም አሣዛኝ ሆኖ ያገኘሁት፤ *"ያለ ግብፅና ሱዳን ይሁንታ ዓባይን መገደብ አግባብ አይሆንም፣ የተታች-ተፋሰስ አገሮችን (ግብፅንና ሱዳንን) የሚጎዳ ስለሚሆን እቅዱ ግብፅን የሚያስቆጣና ጦርነትን የሚጋብዝ ነው"* የሚለው ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በማያያዝም የግብፅንና የኢትዮጵያን የጦር ኃይሎች በማወዳደር "ወዮልን" ዓይነት ማስጠንቀቂያ እስከማስተጋባት ተደርሷል። ግድቡን ለመቃወም ይኸንን የመከራከሪያ ነጥብ ለሚያቀነቅኑ ወገኖቾ የማቀርብላቸው ተያያዥ የሆኑ ሁለት ጥያቄዎች ብቻ አሉኝ።

አንደኛ፤ ኢትዮጵያ በአገርዋ ውስጥ ያለ ሃብቷን ለመጠቀም የውጭ አገርን ፈቃድና ይሁንታ ማግኘት አለባት ማለት ኢትዮጵያ እንደ አገር ያላትን ነፃነት የሚገፍ፣ የሕዝቧንም ሉዓላዊነት የሚፃረር፣ አገራዊና ሕዝባዊ ክብርና ኩራትን የሚዳፈር አይደለም ወይ?

ሁለተኛ፤ እንዲያው እንደተባለው ግብፅ (ሱዳንም ጭምር) በዚኸ ግድብ ምክንያት ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ቢያውጁና ቢዘምቱብን "ወያኔ ያመጣው ችግር ስለሆነ" አያገባኝም ሊሉ ነው? ወይንስ ከእነሱ ጋር ሊሰለፉ? መልሱን ለተቃውሞአቸው ያንን ምክንያት ለሚያቀርቡ ወገኖች ኅሊና ልተወው።

በተወሰነ ደረጃ ይኸ አስተሣሰብ የሚመነጨው ዓባይ ለኢትዮጵያ ያለውን ስትራቴጂካዊ ትርጉም ከመዘንጋትና ይኸን የኅዳሴ ግድብ ከተራ የኤሌክትሪክ አመንጪ ግድብ ውጭ ካለማየት ሊሆን ይችላል። በአሁኑ ጊዜ የዓባይን ግድብ ከተራ ግድብነት ውጭ ያለማየቱ አባዜ ከአሁን በፊት በአንዳንዶቻችን ኢትዮጵያ በቀይ-ባሕር በኩል የራሷ ይዞታና በሙሉ ባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር-በር የግድ ያስፈልጋታል ሲባል ከአገራዊ ደኅንነት፣ ከብሔራዊ ፀጥታና ከኅልውና አኳያ እንደሆነ ካለመገንዘብ፣ *"ከጅቡቲ ይልቅ የኤርትራ መንግሥት አሰብን በነፃ መጠቀም የምንችልበትን ሁኔታ እንዲፈጥር ጥረት ቢደረግ ..."* በሚል ያንን የባሕር-በር ስትራቴጂካዊ አስፈላጊነት ከሽቀጣ-ሸቀጥ ማስተላለፊያ ጎኑ ሊኖረው ከሚችል ጠቀሜታ ውጭ ማየት ካለመቻል ይቀርብ ከነበረው አስተሣሰብ ጋር ይመስላል።

ኢትዮጵያ የጀመረቻቸውን ግድቦች "ያለ ግብፅ ይሁንታ እንኳን መገንባት ማሰብም የለባትም፣ ያ ካልሆነ ግብፅ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት መክፈቷ አይቀሬ ነው" የሚለው ክርክር ግብፅ የዓባይን የውሃ ሃብት እስካሁን ስትጠቀምበት ከነበረው አልፋ በረሃዎቿን ለማልማት ትችል ዘንድ ኢትዮጵያ እጆቿን አጣጥፋ የበይ-ተመልካች ሆና መቀመጥና እንደስካሁኑ ዓባይ የኢትዮጵያ የጥቃት መሥመር ሆኖ መቀጠሉ ተገቢ ነው ከማለት ውጭ ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያ የዓባይን የውሃ ሃብት የመጠቀም ሙሉ መብት አላት። ግብፅም ሆነች ሱዳን ኢትዮጵያ ስትደማ እንድኖር እስካሁን ይዘውት የቆዩትን የተለመደ አቋምና ፖሊሲ ለማስቀጠል መፍቀዱ ተገቢ ነው ካልተባለ በስተቀር በዓባይ መገደብ ምክንያት ግብፅም ሆነች ሱዳን የሚጎዱበት የጎላ ምክንያት የለም። የግብፅና የሱዳን መሪዎችም ሆኑ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሱ ይኸንን ሃቅ በሚገባ ያውቁታል።

በተጨማሪም በኅዳሴው ግድብ መገንባት ሁለቱ አገሮች ከዓባይ የምሚያገኙት የውሃ መጠን በአስተማማኝ እንዲቀጥል ከማድረግ ውጭ እንደማይሄድና የሁለቱም አገሮች ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ እንደሚረዳ አሣምረው ያውቁታል።

በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ በሁለቱም አገሮች በኩል ያሉ መንግሥታት ያለባቸውን የውስጥ ውስብስብና ከባድ ችግሮች በቀላሉ ሊመልሷቸው የማይችሉ በመሆኑ የየአገራቸው ሕዝብ የሚያቀርበውን ጥያቄ ለማድበስበስና አቅጣጫ ለማስቀየር ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ የጀመረችውን ግድብ የመሥራት እቅድ በግልጥም ባይሆን በተዘዋዋሪ ለመጠቀም ሊያስቡ ይችላሉ። ጉዳዩ ደግሞ የሕዝብን ስሜት በቀላሉ ለመቀስቀስ አመቺ በመሆኑ የግብፅና የሱዳን መንግሥታት ብቻ ሣይሆኑ በኢትዮጵያም ያለው አገዛዝ ተመሣሣይ የአደጋ ደወል ሊያሰማ መቻሉ አጠያያቂ አይሆንም። እንደዚኸ ዓይነቱ አካሄድና በዚኸ መንፈስ ለጊዚያዊ የፖለቲካ ጠቀሜታ የሚወሰድ እርምጃ ግን መዘዙ ወደ-በዛ ችግር ውስጥ እንደሚከታቸው

መንግሥታቱ ስለሚያውቁ ወይም ማወቅ ስለሚኖርባቸው፣ ቢበዛ ሊቆጣጠሩት በሚችል መልክ ሕዝብ ስሜቱን እንዲገልጥ ለማድረግ መሞከራቸው አይቀርም።

የኀዳሴው ግድብ እቅድ ድንገት ብቅ ያለ ዱብዳ እንዳልሆነም ግልጥ ነው። የአፄ ኃይለ-ሥላሴ መንግሥት በዓባይ ላይ ግድብ ለመሥራት ከመመኘትና ከማሰብ አልፎ በቁርጠኝነት ተግባራዊ ለማድረግ ጥናት እስከማስደረግ እንደደረሰ፣ በጦርነት ወከባ መኻልም እንኳ ሆኖ ደርግም አሣቡን ትኩረት ሰጥቶት እንደነበር ግልጥ ነው። ቀደም-ሲል ለማቅረብ እንደሞከርኩት፣ የዓባይ ጉዳይ ከባድና ውስብስብ ነው። ዓባይ የኢትዮጵያ ስስ ብልት ነው ማለት ይቻላል፤- በጣም በጥንቃቄና በእንክብካቤ የሚያዝ ጠቃሚ የአገር አካል። በመሆኑም በእሱ ላይ የሚወሰድ ውሳኔ በተራ የፖለቲካ ስሊት ላይ ተመርኩዞም ሆነ ብድግ ብሎ በዘፈቀደና በስሜታዊነት አዋጅ በማስነገር የሚደረግ አይደለም። ተቃውሞ ሲቀርብ አንደኛ የምንቃወመውን ነገር ዓይነት፣ ይዘትና ክብደት በቅጡና በተገቢ መመዘን፤ ሁለተኛ እኔ በዚኽ ጉዳይ ላይ መወሰን ቢኖርብኝ ምን መንገዶችን ልከተልና ምን ዘዴዎችን ልጠቀም ይገባኝ ነበር ብሎ መጠየቁ አስፈላጊ ይመስለኛል።

በእርጥ ከሌላ ሣይሆን ከአገዛዙ ታሪክና ከሚከተለው የፖለቲካ ፍልሥፍና በመነሣት ከእኔው ጀምሮ ለብዙዎች ሕወሓት/ኢሕአዴግ ዓባይን የመገደብ ዓላማም አጀንዳም ይኖረዋል የሚል ግምት እንዳልነበር አጠራጣሪ አይመስለኝም። ሃቁ ግን ይኽ እቅድ ይፋ ከመደረጉ በፊት ከዲፕሎማሲ አንስቶ የግድ መሠራት የነበረባቸው የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች ከ1999 ዓ/ም (እ.አ.አ) የ'ናይል ቤዚን ኢንሺየቲቭ' የተሰኘውን የዓባይ ተፋሰስ አገሮች የምክክር መድረክ ከማቋቋም ጀምሮ በየደረጃው ሲሠሩ ቆይተዋል።

ስለዚኽ ከጉዳዩ ከፍተኛ ጥንቃቄና ተገቢ ቅድመ-ዝግጅትን ከመጠየቁ ባኀሪ አንፃር፤ ይኽ እቅድ ይፋ ሣይወጣ መቆየቱና መሠረታዊ የሚባሉ ዝግጅቶች አስተማማኝ ሲሆኑ ብቻ ገሃድ ማውጣቱ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት አካል ግዴታ ይሆናል። በበኩሌ ባደረኩት ክትትል ሂደቱ ከዚኽ ውጭ ሆኖ አላገኘሁትም። በዚኽ ጉዳይ ላይ አገዛዙ ሊወቀስም፣ ሊነቀፍም ይገባው የነበረው ያለ-ምንም መሠረታዊ ዙሪያውን-ያዬ ጥናትና ቅድመ-ዝግጅት ዓባይን እገድባለሁ ብሎ ቢያውጅ ነበር። አጋጣሚ ሆኖ ግን በወቅቱ የተከሰቱ አካባቢያዊና ዓለም-አቀፍ ሁኔታዎች የተባሉትን ጥርጣሬዎች በብዙዎች ዘንድ ሊፈጥሩ ችለዋል።
እዚኽ ላይ መዘንጋት የሌለበት፤ ምንም እንኳን የአገዛዙ መሪዎች እነሱ ከሚያስቡት ወጣ ያለ አስተሣሰብን ለመቀበል ያላቸው ሥነ-ልቦናዊ ዝግጁነት በአሉታዊ ጎኑ ቢታወቅም፤ በኢሕአዴግ ውስጥም ይሁን ከውጭ-ጉዳይ ጀምሮ በልዩ-ልዩ የአገሪቱ መሥሪያ ቤቶች ያሉ አገር-ወዳድ ሙያተኞች በእንደዚኽ ዓይነት አገራዊ ጉዳይ ላይ በየአጋጣሚው ሊኖራቸው የሚችለውን አስተዋፅዖ በደንብ መገንዘቡና አለመርሳቱ አስፈላጊ ይመስለኛል።

ለነገሩ በዚኽም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ ተቃውሞም ሆነ ድጋፉ ሲበዛ ስሜታዊ፣ እራስን ያልጠየቀና ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ያዬ መሆኑ ግልጥ ነው። በአብዛኛው ተቃዋሚው በኩል ምንም-ይሁን-ምን ነገሮችን አገዛዙን ከሚያዩበት መነፅር አኳያ የመሆኑን ያኽል፣ በአገዛዙም  በኩል የሚቀርብን ተቃውሞ ቆም-ብሎ የራሣቸውን ኀፀጽ ሣያዩ ሮጠው “ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-አገር፣ ፀረ-ልማት፣ ወዘተ” የሚል ስያሜን በጭፍን መለጠፍና ኢትዮጵያ የእነሱ ብቻ እንደሆነች በመቁጠር እነሱ ብቻ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪና አሣቢ ሆነው ለመቅረብ እንደሚዳዱ ግልጥ ነው። ኢትዮጵያና የሕዝባችንን ዘለቄታዊ ጥቅሞች ጉዳይ ግን የአገዛዙ ወይንም የተቃዋሚው ብቻ እንዳልሆነ ግልጥ ሊሆን ይገባል።

የአገራችንን መሠረታዊ ችግሮች ሁሉንም ሊጠቅም በሚችል ሁኔታ ለመፍታትና ኅብረተሰባችንን ከአምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓቶች አዙሪት በማውጣት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚወስድ የሰከነ ሽግግር ለማድረግ አስቸጋሪ የሆነውም ይኽ ተቃውሞን መሠረት ያደረገ አመለካከትና አቋም ነው ማለት ያስደፍራል። ያ ደግሞ መሠረቱ በሁለቱም ተፃራሪ ጎራዎች (በገዥው ክፍልና በተቃዋሚው በኩል) ያሉት ሠልፈኞች የአንድ ትውልድ

*ግኝቶችና ነገሮችን 'እኔ እንደማስበው ካላሰብክና ከእኔ ጋ ካልቆምክ ጠላት ነህ' በሚል እምነት ፍጻሜው መጠፋፋትን እንጂ ልዩነትን ማክበርና ብሔራዊ-መግባባትንም ሆነ በእሱ ላይ የተመሠረተ አገር-አቀፍ እርቅና ሰላም እንዲኖር በማያስችል "በሚታረቅና በማይታረቅ ቅራኔ" የኃይል አሠላለፍ አፈረጃጀት የሚመራ የፖለቲካ ቅኝት ያራመዱና ከዚያም ተመሣሣይ የመጠፋፋት አመለካከትና ሥነ-ልቦና መውጣት ያልቻሉ በመሆናቸው ይመስለኛል::*

*ዞሮ-ዞሮ ለማንም በተገቢ ግልጥ መሆን ያለበት ጉዳይ ዓባይን በኢትዮጵያ ምድር ላይ የመገደብና ያለመገደብ ውሳኔ የኢትዮጵያውያን እንጂ በምንም መንገድ ለሱዳን፣ ለግብፅም ሆነ ለሌላ የውጭ ኃይል አሣልፎ የሚሰጥ አለመሆኑን ነው::*

*የማንኛውም መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃና መሠረታዊ የሚባለው ኃላፊነት የዜጎችን ደኅንነትና ሰላም ማስከበር ነው:: የአንድ አገር ሕዝብ ለሰው-ሰራሽ ችግር የሚጋለጠው ይኸንን በጣም መሠረታዊ የሆነ ኃላፊነት መወጣት የሚችል አስተዳደር ካለመኖሩ የሚመጣ ከመሆን አይዘልም:: ለአጠቃላይ አዋራጅ ድኅነት፣ በተለይም ሰብዓዊ ክብርን ለሚገፍ የምግብ እጥረትና አሰቃቂ የረሃብ አዙሪት ችግሮች የተዳረገ ሕዝብ ስለ ሌሎች መብቶች መከበርና ስለ መልካም አስተዳደር የሚጨነቅበት ጊዜም ፋታም እንዳይኖረው አስተዋፅዖ ያደርጋል:: ይኸንን ሃቅ በመገንዘብም ይመስላል አንዳንድ የመንግሥት ሥልጣን የሚይዙ ገዢ ክፍሎች ሕዝባቸውን ሆን-ብለው እንደ ረሃብ ለመሰለ አሰቃቂ ችግር በመዳረግ ከፍተኛ ኢ-ሰብዓዊ ወንጀል የሚፈጽሙት:: ያ ዓይነት ኅሊና-ቢስ አስተሣሰብ የተጠናወታቸው ገዥዎች ቅድሚያ የሚሰጡት የያዙትን ሥልጣን እስከ-ቻሉ ድረስ እንደምንም ሙጥኝ ብለው ማቆየት ስለሆነ ለሕዝብ ሰብዓዊ-ክብርና መብት መጠበቅም ሆነ ለተጫነበት ጠኔ፣ ሰቆቃና ችግር መወገድ ደንታ አይኖራቸውም::*

*ይኸ የኅዳሴ ግድብ ለመስኖ ሣይሆን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የታሰበ በመሆኑ እዚኸ ላይ ስለ ረሃብና ችግር መወገድ አስፈላጊነት ሲነገር 'ምን አገናኘው?' የሚሉ ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ::*

*ጉዳዩ እንዲኸ ነው፣ አንደኛ አዎን ይኸ የኅዳሴ ግድብ ለመስኖ አገልግሎት ሣይሆን ለመብራት ኃይል (ለኤሌክትሪክ) ማመንጫ ነው የሚሠራው:: ሆኖም ወደ-ኋላ ላይ እንደምናየው ይኸ ግድብ ብቻውን ተነጥሎ የቆመ አይደለም:: ከዚኸ ጋር ቢያንስ አምስት ተያያዥ ግድቦች ይኖራሉ:: ከነዚኸ ውስጥ ግልጋሎታቸው ለመስኖ ብቻ የሆኑና ቅልቅል-አገልግሎት-ሰጭ የሆኑ ይገኙባቸዋል:: ሁለተኛ እንደ-ኢትዮጵያ ለጊዜው በጥቅም ላይ የዋለ የነዳጅ ሃብት (ዘይት/ጋዝ) ለሌለው አገርና ጫካዎችን ለማገዶ ሲባል በመመንጠርም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች የሚከሰት የአየር ብክለትን መከላከል ለሚፈልግ አገርና ኅብረተሰብ፣ እንዲሁም ፈጣን የባቡር አገልግሎት ለመዘርጋትና ጥቅም ላይ ለማዋልም ሆነ ሌሎች የልማት ሥራዎችን ለማስፋፋትና ሕዝብን በስፋት ተጠቃሚ ለማድረግ የኤሌክትሪክ ኃይል ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም:: እዚኸ ላይ ግልጥ መሆን ያለበት የብዙዎች ክርክር ይኸን የኅዳሴ ግድብም ሆነ እንደ ግቤ አይነቶቹን ግድቦች የሚመለከቷቸው ከእነኝኸ ግድቦች የሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ-ውጭ አገሮች ተሽጦ ሊያስገኝ ይችላል ከሚባለው ገቢ አኳያ ብቻ እንጂ ከእነዚኸ ግድቦች የሚመነጨው ኃይል በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰጡት የሚችሉትን ሠፊ የኤሌክትሪክ አውታሮች ዝርጋታና ኤሌክትሪክ-ተኮር (ኤሌክትሪፊኬሽን) አገልግሎትን ጨርሶ የዘነጋ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::*

*ስለሆነም ከዓባይ ላይ ከሚገደበውም ሆነ ከሌሎቹ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች የሚመረተው ኃይል ወደ-ውጭ አገሮች ተሽጦ ከሚያስገኘው የገንዘብ ገቢ ይበልጥ (ቢያንስ ያልተናነሰ) በአገር ውስጥ ከመሠረታዊ የመብራት ፍጆታ ጀምሮ ከትንሽ እስከ ትላልቅ አገልግሎት-ሰጪ ኢንዱስትሪዎችን ለማንቀሣቀስ የሚኖረው ምትክ-የለሽ አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም:: ከዚኸም በላይ ምንጩ ከውጭ ሣይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ*

አገልግሎቱ በፖለቲካ ምክንያት አገርን ለመጉዳት ከማሰብም ይሁን ተጨማሪ ክፍያ ለማግኘት ሲባል ድንገት የማይቋረጥና አስተማማኝ፣ ለባዕዳን ጥገኛ የማያደርግና ለእነሱም ተፅዕኖ ያላጋለጠ ጠቀሜታ እንዳለው ሊታወቅ ይገባል:: በአኳያውም ከዚኽ ኅዳሴ ግድብ ከሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ የሚሆን የውጭ አገር ሁሉ ኢትዮጵያን ባይወድም እንኳ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥበት ሲል ብቻ ቢያንስ የከፋ ከማሰብ እንዲቆጠብ ስለሚገድድ ከጎረቤቶች ጋር ሰላም እንዲኖር፣ አልፎም ይኽ በጥቅም ላይ የተሣሰረው ግንኙነት ወደ-ሌሎች የመተባበሪያ መሥመሮች ሊያድግና በሰላም አብሮ ለመበልፀግ ወደ-ማሰብ ሊወስድ ይችላል:: ይኽ እያደገና እየሰፋ ሊሄድ የሚችል በጥቅም መተሣሰር ደግሞ ለአካባቢያዊ ሰላም የሚኖረው አስተ‌ጋብዖ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም::

እንደ አንድ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሚከተሉት ምክንያቶች ይኽ የኅዳሴ ግድብ መደገፍ እንደሚኖርበት እምነቴ ነው:: <u>በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ውስጥ በዓባይ ላይ ግድብ ለመሥራት ለኢትዮጵያ ከዚኽ ጊዜ የተሻለ የአካባቢና የዓለም-አቀፍ ሁኔታ ኖሮ አያውቅም ማለት ይቻላል::</u> ሁኔታውን በቅጡና በወቅቱ መጠቀም ካልተቻለ እነዚኽ ጊዜው ያስገኛቸው መልካም ሁኔታዎችና በጎ አጋጣሚዎች ሊቀየሩ መቻላቸው ሊታወቅ ይገባል:: ስለሆነም፣ ኢትዮጵያ ዓባይ ላይ ትርጉም ያለው ግድብ መሥራት ከፈለገች ደግሞ - መፈለግ ብቻ ሣይሆን የማድረግ ግዴታም አለባት - <u>ወቅቱ አሁን ነው::</u>

ኢትዮጵያውያን እንደ-ሕዝብ ይኽንን መሰል-የሌለው ሁኔታ በወቅቱ ካልተጠቀምንበት፣ ስለ ዓባይ ጉዳይ በቁጭት ከመንገብገብና የወደፊት ተከታታይ ትውልዶችን ዕድል እንደዘጋን፣ የእነሱንም ይቅርታ የሌለው ምሬት እንደምናተርፍ ሊታወቅ ይገባል::

ለምን?

**ሀ) የተቀየረው አካባቢያዊና ዓለም-አቀፍ ሁኔታ የሚያስገኘው ጥቅም፤**

1. የቅኝ-ገዥዋን የእንግሊዝን እግር በመከተልና ተመሣሣይ አቋም በመያዝ በዓባይ ውሃ አጠቃቀም ወሣኞች በዋናነት ግብፅና በቀጣይነት ሱዳን ሆነው መቆየታቸው ይታወቃል:: ምንም እንኳን የዓባይ ተፋሰስ አገሮች በርካታ ቢሆኑም፤ የዓባይን የውሃ ሃብት አጠቃቀም በተመለከተ ግን ሙሉ የወሣኝነትን መብት ለግብፅና ለሱዳን አሣልፎ እንዲሰጥ ሲደረግ አብዛኞቹ በእንግሊዝ ቅኝ-ግዛት ሥር ስለነበሩና ሁኔታው ስላልፈቀደላቸው ድምፃቸው ታፍኖ መቆየቱ ይታወቃል:: ይኽን በቅኝ ገዥዎች እብሪትና ተንኮል በፍርደ-ገምድል ብይን የተወሰደ አቋም ከመጀመሪያ ጀምሮ የተቃውሞ ድምፅ ማሰማቷን ያላቆመችና የዓባይን ውሃ ለመጠቀም ተደጋጋሚ ጥረቶች ያደረገች ኢትዮጵያ ብቻ ሆና ቆይታለች::
ምንም እንኳን በዓባይ ጉዳይ እስካሁን ኢትዮጵያ ብቻዋን ቆማ መቆየቷ ቢታወቅም፤ በአሁኑ ጊዜ ያ ሁኔታ ለኢትዮጵያ በአዎንታዊ መልኩ ተቀይሯል:: በአሁኑ ጊዜ ሌሎች የዓባይ ተፋሰስ-አገሮች ከኢትዮጵያ ጋር መሰለፍ በመቻላቸው፣ የዓባይ ውሃ አጠቃቀም ጥያቄ በአንድ በኩል ግብፅና ሱዳን በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ብቻዋን ከመሆን አልፎ የምሥራቅ-አፍሪቃ ጉዳይ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል::
የዓባይን ውሃ በእኩል መጠቀም ስለሚቻልበት ለመምከርና የወንዞቹን (ነጭና ጥቁር ዓባይ) ተፋሰስ አካባቢ *'በጋራ ለማልማትና ከልማቱም የሚገኘውን ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ግኝት በጋራ ለመጠቀም'* በ1999 ዓ/ም (ኢ.አ.አ.) ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ግብፅ፣ ዩጋንዳ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ቡሩንዲ፣ ሩዋንዳና የኮንጎ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በጋራ ተስማምተው *'የናይል ቤዚን ኢኒሺየቲቭ'* በሚል መጠሪያ የጋራ የምክክር መድረክ ካቋቋሙና ይኽም በዓለም ባንክ ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ካገኘ ጊዜ ጀምሮ ቀደም ሲል በግብፅና በሱዳን ብቸኛ ፈቃድና እስትንፋስ ሲወሰን የቆየው የዓባይ ጉዳይ የማክተሚያውን ደወል በገሃድና በማያሻማ መልኩ ማሰማት መቻሉ፣ በዚኽም በዓባይ ጉዳይ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻዋን መሆኗ እንዲያከትም መደረጉ የመጀመሪያው አዲስ በጎ ክስተት ነው::

2. ቀደም-ሲል የቅኝ-ገዥዋ እንግሊዝ ከዚያም ነፃነታቸውን ካገኙ በኋላ ግብፅና ሱዳን፣ በተለይና በዋናነት ግን ግብፅ በአካባቢውና በዓለም-አቀፍ ደረጃ በነበራት ተደማጭነት ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ለመጠቀም እንዳትችል ከማንኛውም የዓለም-አቀፍ ተቋምና የመንግሥት አካል ብድር እንዳታገኝ በሩ ሁሉ እንዲዘጋ ከማድረግ ጀምሮ ልዩ-ልዩ ጫናዎችን ማሣደር በመቻሏ ፍላጎት ቢኖራት ኢትዮጵያ በዚኽ የገንዘብ ችግር ምክንያት አቅመ-ደካማ ሆና ምኞቷ ተዳፍኖ እንዲዘልቅ መደረጉ ይታወቃል፡፡ ይኽ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመ በደል ሊረሣ የማይችልና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በምሬት ሊያስታውሰው የሚገባ ግፍ ነው፡፡ (በዚኽ ረገድ በተወሰነ ደረጃ ሱዳንም ሚና እንደነበራት ግልጥ ነው)፡፡ ይሁንናም በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ በአንድ በኩል በራሷና በሌላ በኩል በተወሰኑ የውጭ እርዳታዎች (በተለይም ከቻይና) በመደገፍ ቀላል የማይባሉ የግድብ ሥራዎችን ማከናዎን መቻሏና የአቅም በሮች ሁሉ ባለመዘጋታቸው እስከ ዛሬ መስበር ያልተቻለውን የግብፅን የብድር ወይም የእርዳታ ማስከልከል ጉልበት በጣም እናግቶታል፡፡

3. ኢትዮጵያ በልማት ሥራዎች ላይ እንዳትሠማራ የውስጥ ሰላሟን እንድታጣና ያላትን ጥሪት በሰላም ማስጠበቅና በአንድነት ማስከበር ጥረት ላይ እንድታውል ዝንታለም ተወጥራ እንደቆየች ይታወቃል፡፡ ለዚኽ ደግሞ ግብፅና ሱዳን ግንባር-ቀደም ከሆኑት ውስጥ እንደነበሩ እሙን ነው፡፡ ምንም እንኳ አሁንም ቢሆን አስገዳጅ ሁኔታዎች የሉም ባይባልም በአሁኑ ጊዜ በእጅጉ መቀነሣቸው ወይም ከአቅም በላይ የማይሆኑ፣ መወጣት የማያዳግቱና አልፎም ማስወገድ የሚያስችል ሁኔታ መኖሩ ለኢትዮጵያ በትላልቅ አገራዊ እቅዶች ላይ ለመሠማራት የተሻለ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

4. የሱዳን ከሁለት መሰንጠቅ፣ የቀረውን አንድነቷንም የሚፈታተኑ በርካታ የውስጥ ችግሮች መኖራቸውና በከፍተኛ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ውጥረቶች መጠመድ - ምንም እንኳን አሁንም የምትችለውን ሁሉ አታደርግም ባይባልም - ሱዳን እንደ-በፊቱ ሙሉ ኃይሏን ኢትዮጵያን በመተናኮል ላይ ለመሰለፍ የምትችልበት ደረጃ ላይ አለመሆኗ ኢትዮጵያ ከዚያ አቅጣጫ ከሚደርስ መተናኮል አንፃራዊ ፋታን እንድታገኝ ዕድል ሰጥቷል፡፡ ከዚኽ በተጨማሪ ኢትዮጵያ በሁለቱም ሱዳኖች (ሱዳንና ደቡብ-ሱዳን) መኻል እንደ-አስታራቂም እንደ-ገላጋይም፣ በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪቃ አንድነት ጥላ ሥር እንደ ሰላምና ስምምነት አስከባሪም መሆን የቻለችበት ሁኔታ በመፈጠሩ፣ የኃይል ሚዛኑ ለኢትዮጵያ ባደላ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይኽ ለኢትዮጵያ የውስጥ ሰላም የሚኖረው አስተዋፅዖ በቀላሉ የማይገመት ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታን ፈጥሯል፡፡ *(ይኽ ሁኔታ ቶሎ ሊቀየሩ ከሚችሉት መኻልና አልፎም ከወዲኹ በጥንቃቄ ካልታሰበበት ያደፈጠ-አደጋ እንዳለ ይገነዘቧል፡፡ በዚኽ ላይ በሌላ ጊዜ አሣብ እሰጥበታለሁ፡፡)*

5. የደቡብ ሱዳን አዲስ አገር መሆን ከግብፅና ከሱዳን ሌላ አብረው የቆሙ የዓባይ ተፋሰስ አገሮችን ቁጥር ከማሳደጉም በተጨማሪ፣ የ'ናይል ቤዚን ኢኒሺየቲቭ'ም ሆነ ከሱ ተያይዘው የተፈጠሩ የጋራ መድረኮችና ተቋሞች ላይ የሚወሰዱ አቋሞችን ከሞላ-ጎደል አስተማማኝ ሊሆን በሚችል መልክ ከኢትዮጵያ ጎን መሰለፍ የሚችል አዲስ 'ወዳጅ' አገር መኖሩ ሌላው ጥቅም ላይ ሊውል የሚገባው አዲስ አዎንታዊ ጎን ነው፡፡

6. የግብፅ እየተወሣሰቡ የሄዱ የውስጥ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ተደራራቢ ችግሮች፣ በአካባቢው የነበራት የጎላ ሚናና ተደማጭነት እየደበዘዘ ከመሄድ ጋር ተደማምሮ ግብፅ በዓባይ ጉዳይ ፍላጎቷን እንዳሻት ለማስፈጸም የነበራት አቅም በመጠኑ የተቀነሰ ሆኗል፡፡ በአካባቢው በተከሰቱና በተለዋወጡ አዳዲስ ሁኔታዎች ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ግብፅ በተለይ በምዕራቡ ዓይን የነበራት 'ምትክ-የለሽና ወሣኝ' ሆኖ ይታይ የነበረ ሚናዋ በነበረበት ደረጃ ላይ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ለአካባቢው የዋዠቀ ሁኔታ መረጋጋት ያላት ጉልኅ ሚና አንፃራዊ ጥንካሬ የሚታይበትና የግብፅ አቅም ግን የነበረውን ያኽል እንዳልሆነና እየቀነሰ የመሄድ ዕድሉ ጠንካራ መሆኑ ሌላው በጎ ጎን ነው፡፡

7. ኢትዮጵያን ሰላም መንሣትና አንድነቷን መፈታተን ቋሚ ተልእኮአቸው አድርገው የቆዩ ተከታታይ የሶማሊ ገዥዎች ከመድረኩ ላይ አለመኖራቸው ብቻ ሣይሆን ይኽቺ ጎረቤት አገር በገጠሚት አሣዛኝ የውስጥ ውጥንቅጥ ሁኔታዎችና ከባድ ችግሮች ምክንያት ቢያንስ ለጊዜው ኢትዮጵያን በቀጥታ ለመተናኮልም ሆነ ቀደም-ሲል እንደነበረው የሌሎች አገሮች ተቀጥላና ተባባሪ በመሆን በኢትዮጵያ ላይ ወጣሪ አዲስ ግንባር መክፈት የማትችልበት ሁኔታ ላይ መሆኗ ኢትዮጵያ ከዚያ በኩል አንፃራዊ ፋታን እንድታገኝ አድርጓል። ይኽም ረዥም ጊዜ ሳይለወጡ ሳይዘልቁ ከሚችሉ አዲስ አዎንታዊ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ሁኔታውን ኢትዮጵያ በአግባቡ ልትጠቀምበት የሚገባ መልካም አጋጣሚ ነው።

8. ጎልውናውን ኢትዮጵያን ከመበጥበጥ ጋር ያቆራኘ የሚመስለው በሸዓብያ የሚመራው የኤርትራ መንግሥት በውስጡ ባለው ከፍተኛ ዙሪያ-ጥምጥም ችግር ምክንያት፤ ፍላጎትና ምኞት ቢኖረውም እንኳን፤ በአሁኑ ጊዜ በራሱ አነሣሽነትም ይሁን የሌሎች የውጭ ኃይሎች ወኪል በመሆን በኢትዮጵያ ላይ ኢትዮጵያ ልትቋቋመው የማትችል ሌላ ወጣሪ ግንባር ለመክፈት የሚችልበት አቅሙ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ደካማ መሆኑ ሌላው መልካም አጋጣሚ ነው። በእርግጥ የሻብያ መሪዎች አሁንም በተለይ በግድቡ መሠራት ላይ ችግር ይኖራቸዋል ተብለው ከሚጠበቁት ሱዳንና ግብፅ ይበልጥ ተቆርቋሪ ሆነው ሲወራጩና የማሰናከል ወኪልና አጋፋሪ ለመሆን ሲራወጡ በአግራሞት እየታዘብን ነው።

9. የኢትዮጵያን አንድነትና የውስጥ ሰላም በልዩ-ልዩ መንገድ ሲተናኮሉና ለሚተናኮሉም ሲያበረታቱና ሙሉ ድጋፋቸውን ሲለግሱ የቆዩ እንደ ሊብያ፤ ሲሪያና ኢራቅ የመሣሰሉት ፀረ-ኢትዮጵያ የአድጎሮት ኃይሎች ከመድረኩ መገለል፤ በዓባይ ግድብ ላይ በቀጥታ ያገባናል ባዮቹና ኢትዮጵያ በዓባይ ውሃ እንዳትጠቀም ሙሉ-በሙሉና ዋነኛ እንቅፋት ሆነው ለቆዩት ግብፅና ሱዳን ሊሰጡት የሚችሉት እርዳታና ትብብር በእጅጉ ከመቀነስ እስከ ጨርሶ መኖር ያለመቻሉ ሌላው ለኢትዮጵያ በእጅጉ ጠቀሜታ ያለው አጋጣሚ ነው። ከዚኹ ጋር "የአረብ ፀደይ" የብዙ አረብ አገሮችን የውስጥ ይዞታ በልዩ-ልዩ ደረጃ ስላናወጠውና በየውስጥ ችግሮቻቸው ተወጥሮ መያዝ በግብፅና በሱዳን ላይ ሊኖራቸው የሚችለው በጭፍን የመወገን ፍላጎትና የመርዳት አቅም ላይ የሚኖረው ጫና አብሮ ሊታይ የሚችል ነው።

10. በአሁኑ ጊዜ ግብፅ በ"እስላም ወንድማማች" መሪ በሙሐመድ ሙርሲ የሚመራ መንግሥት ሥር መሆኗ የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡ (በተለይም የምዕራቡ ዓለም) ለግብፅ ያለው አመለካከት በጥርጣሬ የተሞላና ለግብፅ የሚደረገው ደፈናዊ እርዳታም እስካሁን እንደቆየው በደፈናው ሳይሆን የመቻል ዕድሉ ሰፊ ነው። በመሆኑም በዓባይ ጉዳይ ላይ የግብፅን ገዥነት ይዞ የኖረው አቋም ሙሉ-ለሙሉና ያለ ጥያቄ ለመደገፍም ሆኖ ካሁን በፊት ይሰጡት የነበረው ለግብፅ ያዳላና የደነደነ ድጋፍ ሊኖር አለመቻሉ፤ ቢያንስ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓባይ ተፋሰስ አገሮች የዓባይን ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ ያላቸውን "በጋራ እናልማና በጋራ እንጠቀም" አቋም ሲሆን ሙሉ-በሙሉ ለመደገፍ ካልሆነም ጆሮ ሰጥቶ ለማዳመጥና ለግብፅ የወገነ አቋማቸው ቢያንስ ቢያንስ ሊቀንስ  የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ቀደም-ሲል ያልነበረም ይሆናል ተብሎም ያልታሰበ መልካም አጋጣሚ ነው።

ከዚኹ ጋር በደንብ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ በአክራሪነት "በሚጠረጠረው" በእስላም-ወንድማማቾች የምትመራዋ ግብፅ የምዕራቡን፣ በተለይም የአሜሪካን ይሁንታ ሳታገኝ ግብፅ በእብሪት ብድግ ብላ ኢትዮጵያ ላይ ወታደራዊ ዘመቻ መክፈት የምትችል አይመስለኝም። ካደረገችም ዘመቻው የተራዘመ ያለመሆን ዕድሉና በግብፅና በምዕራቡ ዓለም መኻል ያለውን ግንኙነት ሊያሻክር መቻሉ አጠራጣሪ አይመስለኝም። አንዳንድ ወገኖች እንደሰጉበት ግብፅ ብድግ ብላ ወታደራዊ እርምጃ መውሰድ አትችልም። ይኽ ማለት አቅሙ የላትም ማለት ግን አይደለም። ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ከመወሰኗ በፊት ግን የተለወጡ ሁኔታዎችንና ብዙ ነገሮችን ማውጠንጠን ይኖርባቸዋል። ግብፆች በተቀየሩ ሁኔታዎች ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ

በሚወሰድ ወታደራዊ እርምጃ ወይም በማስፈራራት በዓባይ ላይ ይዘውት የቆዩትን ወሳኝነት ጠብቆ ማስቀጠልም ሆነ ከዓባይ የሚያገኙት ውሃ ላይ ዋስትና ሊያስገኝላቸው እንደማይችል አልፎም በራሣቸው ዘለቄታዊ ጥቅም እንደዘመቱ በተገቢ ሊያውቁት ይገባል፡፡ ዞሮ-ዞሮ ግን ለዓባይ ግድብ እውን መሆንም ሆነ በግብፅ በኩል ይደርሳል ተብሎ የሚሰጋበትን ማንኛውንም እርምጃ የሚያስቀረው በአገር-ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ-ሕዝብ በዓባይ መገደብ ላይ ያለውን የጠና እምነትና ዝግጁነት በአንድንነትና በአገር-ወዳድነት መንፈስ በተግባር ማሣየት መቻል-አለመቻሉ ይሆናል፡፡

11. ቻይና በኢትዮጵያ ያላት ከፍተኛ ጥሪት የማፍሰስና በብዙ እንቅስቃሴዎች ላይ የጎላ ተሣትፎ ማድረጓ፣ ኢትዮጵያ ለአካባቢው ካላት ቁልፍ ሚና አኳያና ቢያንስ-ቢያንስ በኢትዮጵያ ላይ ያፈሰሱትን ጥሪት እንዳይባክንና የረጅም ጊዜ ጥቅማ-ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ እንደ ተባበሩት መንግሥታት ባሉ ዓለም-አቀፍ መድረኮች ላይ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፋቸውን የመስጠትም ሆነ ገንዘብ በማበደር በኩል የሚኖራቸው ሚዛን-ደፊ ሚና በሁለት መልኩ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡ በአንድ በኩል ግልፁ የሆነው ኢትዮጵያ ከቻይና የምታገኘው የፖለቲካ፣ የቴክኖሎጅና የገንዘብ እርዳታ ሲሆን፤ ሁለተኛው ያ ዓይነት ሥር-የሰደደ ቁርኝት ቻይና ከሌሎች የአካባቢው አገሮች፣ በተለይም ከግብፅ ጋር፣ ያላት የቆየ ግንኙነት ላይ የሚያሣድረው ተፅዕኖ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ቻይና ከግብፅ ጋር የነበራት ሠፊ የንግድ ግንኙነት እንዳለ ሆኖ፣ ግብፅ ኢትዮጵያ ለምትሠራቸው ግድቦች፣ በተለይም በዓባይ ግድብ ላይ ቻይና ተሣትፎ እንዳታደርግና ድጋፍ እንዳትሰጥ ያደረጉት ሙከራ ሁሉ አለመሣካቱ የሚያመለክተው፣ በአንድ በኩል የቻይናን አሻሚነት የሌለው ምርጫ፤ በሌላ በኩል የግብፅ በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ለማሣደር ያላትን አቅም እየቀነሰ መሄድ በተገቢ የሚያመላክት ነው፡፡ ይኸም ለኢትዮጵያ ያለው ጠቀሜታ ግልፁ ይመስለኛል፡፡

12. ቻይና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያላት ባለ-ብዙ ፈርጅ ግንኙነትና ትስስር ይበልጥ ሥር እየሰደደ መሄዱ ቻይና በኢትዮጵያ ብቻ ሣይሆን በአካባቢው ሊኖራት የሚችለው እየተጠናከረ የሚሄድ ይዞታ የሚያሳስባቸውና አልፎም ስጋት የሆነባቸው የምዕራቡ አገሮች በአሁኑ ጊዜ ባለው እጅግ የዋዠቀና አደገኛ የአካባቢ ሁኔታ በማኩረፍ ኢትዮጵያን እርግፍ አድርጎ መተውና ሌላ አማራጭ ለመደገፍ የሚችሉበት አጋጣሚ ስለሌለ፣ ቢያንስ ላልተወሰነ ጊዜ “የተሻለ ወዳጅ” ሆኖ ለመታየትም ሆነ የኢትዮጵያን “ወዳጅነት” ላለማጣት የዲፕሎማሲ፣ የፖለቲካና የፋይናንስ ድጋፍ ለመለገስና ከተቻለ 'በካሮቱ' ወዳጅነትን ለመግዛት የመጀመሪያው ምርጫቸው እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ያም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የምዕራቡ ኃያላን ኢትዮጵያን የሚጎዱ እርምጃዎችን ከሚወስዱ ወይም ሊወስዱ ከሚያስቡ ጋር ላለመቆም የሚገደዱበት ሁኔታ ያለ ይመስለኛል፡፡ በነዚኽ ተደጋጋፊ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ከሁለቱም ወዳጅነትን ለማግኘት፣ ቢያንስ ግን ግልፁ የሆነ የጠላትነት ስጋት ሊኖርባት ያለመቻሉ አጋጣሚ የሚፈጥረው ጊዜያዊ ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡

13. የዓባይ ተፋሰስ አገሮች ዓባይን በጋራ አልምቶ ከውጤቱ (ከግኝቱ) እኩል ተጠቃሚ ለመሆን የወሰዱት የጋራ አቋም እያንዳንዳቸው ባቀዱትና በጋራ ስምምነት ተግባራዊ የሚሆኑ እቅዶች ውጤት ማስገኘት ሲጀምሩ ለእያንዳንዱ አገር በተናጠል ከሚያስገኘው የልማት ጠቀሜታ በላይ ይኸ የመተባበር ስሜት በመኻላቸው የሚፈጥረው የተሻለ መተማመንና መቀራረብ ትብብሩን ቢያንስ ወደ-ላቀ የፖለቲካ ትስስር የሚወስድ የጋራ የኤኮኖሚ ስብስብ እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ሊያስገኝ የመቻሉና በአካባቢው ሰላም እንዲሰፍን የሚኖረው ከፍተኛ አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡ ይኸ ደግሞ ለኢትዮጵያ ልማትና እድገት እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የውስጥ ሰላም በማስገኘቱ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በዚኽ ረገድ የኅዳሴው ግድብ ከሚያመነጨው ኃይል ተጠቃሚ በሚሆኑ አገሮች መኻል የሚፈጠረው መቀራረብ ለቀጣይ ትብብሮች በጥሩ ምሣሌነት እንደሚጠቅም መገመት ይቻላል፡፡

**በክፍል ሦስት ይቀጥላል፤.....**